**ቅኔ በየዘርፉ!**
ገሞራው (ከሀገረ ስዊድን)

ቅኔ የብዙኃን ሐሳባውያን ይዘቶች መግለጫ ነው። በዚህም ልዩ ባሕርዩ የማይደርስበት አድማስና የማይገባበት ፅንፍ የለም። በዚህ ዓለም ውስጥ የቅኔ አውታራዊ አዕጋር ተራምደው ሊቃኙት የማይ ቻሉ አንዳች ነገሮች እንደማይኖሩ ሁሉ፣ የትም የት ደርሶ የሚያጋጥሙትን ሐሳቦች ሁሉ የመግል ጽ ልዩ ኃይል አለው። በዛሬው የቅኔ አቅርቦት ክፍለ ጊዜ ወደ ተክሎች ፍሬያት ጎራ ብዬ ጉብኝ ት አደርጋለሁ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ሁሉ በገፀ ምድር ላይ የተለያዩ ፍሬያት ይገኛሉ። ሀ ገራችንም ልዩ ብሔረ-ዕፀዋት በመሆኗ የተለያዩ ፍሬያት አሏት። በቅርብ ከምናውቃቸውና አዘውት ረን ከምንመገባቸው ፍሬያት ላይ ብንነሳ እነ ሙዝ፣ ፓፓዬ፣ ትርንጎ፣ መንደሪን፣ በትረ ሎሚ፣ አ ውጥ .... ይገኛሉ። እነዚህም ሁሉ ፍሬያት፣ ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት የየግላቸው ቅርጽና ቀለ ም፣ መዓዛና ጣዕም፣ ሌላም ባሕርያት አሏቸው። በዓይነት ቁጥራቸው ብዙኃን ስለሆኑ፣ ሁሉንም መዘርዘር አይቻልም። ዛሬ የማቀርብላችሁ ቅኔ፣ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ፍሬያት ውስጥ አትገኝ ም። በሁለንተናዋ ከሁሉም የተለየ ባሕርይ ያላት የፍሬ ዓይነት ናት። ደመ ክርስቶስ የምትሆነዋ ዕፀ ወይን እንዳትመስላችሁ። በለስም አይደለችም። ማን እንደሆነች የዛሬውን ቅኔ ስታዳምጡ ታውቁታላችሁና ወደ ቅኔው ልውሰዳችሁ።

## ቅኔ ዘብርቱካን

1. ፍሬያት በሙሉ - አላቸው ባሕርይ፣
ምንነታቸውን - ለይቶ የሚያሳይ።
ሙዝም ለስላሴ ናት - ሎሚቱም ኮምጣጣ፣
ሌላም ፍሬ ቢሆን - አለው የግል ጣጣ።
በጣዕም በሽታ - ባላት ልዩ ግርማ፣
ከሁሉም ፍሬያት - ውብ እንደ ቄጠማ፣
ያች ብርቱካን ናት - ልብ የምትስማማ!!

****************************

2. እያንዳንዱ ፍሬ - አለው ልዩ ጠባይ፣
የግሉ የሆነ - ከሌላው የሚለይ፣
ከሁሉም ከሁሉም - ከሁሉም ፍሬያት፣
የሰው ልጆች ሁሉ - ቀምሰው የረኩባት፣
ተክለ ሕይወቷ ዕፅ - ያች ብርቱካን ናት።

********************************

3. በሥነ ፍትሕ ሚዛን - ከሁሉም ተመርጣ፣
ከፍሬያት ሁሉ - ውበት አንቆጥቁጣ፣
ወርቁን የለበሰች - አካሏን አስጊጣ፣
ከሁሉም ፍሬያት - የሰው ልጅ ያወቃት፣
ዓለሙ በሙሉ - እጅግ ያደነቃት፣
ወገን ያመነባት - ያች ብርቱካን ናት።

********************************

4. ወደ አገሬ ኢትዮጵያ - ብትኖሩ እምትሄዱ፣
ከበሸበሸ ፍሬዋ - ካለው በያፀዱ፣
ከዬትም ገብታችሁ - እሷ ካለችበት፣
እድሉ አጋጥሟችሁ - ድንገት ብታገኙዋት፣
ይዛችሁልኝ ኑ - በምስጢር በሽፋን፣
ናፍቃኛለችና - ጣፋጯ ብርቱካን!!

***********************************

Posted on www.debteraw.com on 27 January 2007 by the courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

5. የፍሬያት ዓይነት - ተደርድሮ ባገኝ፣
የመምረጥም ቅድሚያ - ዕድሉ ቢሰጠኝ፣
ተሰልፈው ካሉት - ከፍሬያት ዓይነት፣
የኔ ልዩ ምርጫ - ያች ብርቱካን ናት።




**********************************

6. የበላሁት ሁሉ - ትርንጎ ፓፓዬ፣
ነበረ ዓይነቱ - የትላንት ምሳዬ፣
ይግረማችሁና - ታምር ነው ባትሉኝ፣
ብርቱካን ብርቱካን - ነበረ ያገሳኝ።

**********************************

7. ገብቼ ስጎብኝ - ከትክለ ፍሬያት፣
ከዚያ ሁሉ ፍሬ - ከሚታይ በብዛት፣
ቀልቤን የሳበችው - የሰጠችኝ ስሜት፣
በሩቁ የማያት - ያች ብርቱካን ናት።

**********************************

8. የእንጦጦ ግርጌ - ብዙ ተክል ያበቅላል፣
ቁጥሩ የማይታወቅ - ፍሬያት ያፈራል፣
ከዚያ ሁሉ ፍሬ - እኔን የማረከች፣
ሌላውን አላውቅም - አንዷ ብርቱካን ነች።

**********************************

Posted on www.debteraw.com on 27 January 2007 by the courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

9. ከፍሬያት ሁሉ - የወርቅ ቀለም ያላት፣
በየአገሩ ሁሉ - ሕዝቦች የሚያደንቋት፣
ጣዕሟ ማራኪ፣ ምንም ዓይነት ወደር - የማይገኝላት፣
ለፍርድም አመች - በይዘቷ ውበት፣
ሰው ያለውን ይበል - እኔ ግን በግሌ፣
የማውቅ ይመስለኛል - እሷን በበኩሌ።
ታሪክ ሳላበዛ - ብናገር ደፍሬ፣
አንዷት ብርቱካን ናት - ያች ልዩ ፍሬ!!

************************************

10. አዬ የጅል ነገር - ሞኛ ሞኝ ገገማ፣
ምንም የማይገባው - ጣፎርዴ ጠማማ፣
ያችን መሳይ ፍሬ - እንጦጦ ሲያገኛት፣
ብርቱካን መሆኗን - ማወቁ ተስኖት፣
ለምለም ቦታ ወስዶ - ለትውልድ ሳይተክላት፣
ገፍቶ ከዘብጥያ - እንዳረም ይጣላት?

*****************************************

11. በዩክራይና - ያን ሰሞን የታየው፣
በያደባባዩ - የተውለበለበው፣
ኦሬንጅ አይደለም ወይ - ብርቱካን ምሳሌው፣
ታዲያ ለምን ይሆን? በዚያ ሀገራችን - ዋጋ ያልተሰጠው?

ማስታወሻ!
በዚሁ መንፈስ ስለ ኲፊ (ቡና)፣ ስለ አውጥ፣ ስለ እንጆሪ ...... ቅኔዎቹ ይቀጥላሉ።

Posted on www.debteraw.com on 27 January 2007 by the courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com